# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

14



ኅዳር ፲፭ — ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# ሽብርን ለመቋቋም

በየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ከፈነዳበት ወቅት አንስቶ አድኃሪና ቀልባሾች በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመጠቀም አብዮታችንን ለመቀልበስ በደማችንና በመስዋዕትነታችን የተቀዳጀናቸውን ድሎች መልሰው ለመንጠቅ ያልሞከሩት የላቸውም ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ከየአቅጣጫው የሚሰነዘሩበትን ልዩ ልዩ ተንኮሎችና ማወናበጃዎች ተራ በተራ እያከሸፈ በአብዮቱ ጐዳና ላይ አንዴም እፎይታ ያላወቀ ጉዞውን ቀጥሎ እነሆ አሁን የምንገኝበት ከፍተኛ የትግልና የድል መድረክ ላይ ይገኛል ።

ከየካቲት በፊት ፊውዶ ፋሽስቱ አገዛዝ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያወረደው ግፍና ስቃይ ይህ ነው የማይባል ደረጃ ላይ ስለነበረ ያ ግፈኛ የኃይለሥላሴ አገዛዝ በአብዮታዊው ማዕበል እየተመታና እየተፍረከረከ ሲወድቅ በቀጥታ «ፊውዶ ፋሽስቱ አገዛዝ ይኑር» ብሎ ሊያድነው የተነሳ ምንም ዓይነት «የረባ» ኃይል አልነበረም ። ይህ ማለት ግን ያ ግፈኛ ሥርዓት እየተጠጋገነ ፤ በሀገራችን ምድር ላይ እንዳንሰራራ እንዲቀይ የሚፈልጉ ተጠቃሚዎቹ አልነበሩም ማለት አይደለም ። ነበሩ ። ነገር ግን በቁጣ የተነሳሱትን ጭቁን ሕዝቦች ፊት አፍና የደም እንባ ሲያስለቅሳቸው የነበረውን የበሰበሰ ሥርዐት በቀጥታ ደግፎ ለመከራከር የሚደፍር ምንም ዓይነት የኅብረተሰብ ክፍል አልነበረም ። -

ስለሆነም አድኃሪ ኃይሎች የኢትዮጵያን አብዮት የማያወላውል ግስጋሴ ለመግታት ፤ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአብዮታዊ ቁጣ ቅስቀሳ ከዳር እስከዳር የተፋፋመውን የመደቦች ትግል ለማፈን ታሪክና ሕዝብ የተፋቸው አድኃሪያን የአብዮቱን ማዕበል ፊት ለፊት ገጥመው ለመቋቋም የሞከሩበት ወቅት የለም ። በየጊዜው በሚጐናጸፋቸው ድሎች የሕዝቡን የደስታ ስሜት ብቻ ሳይሆን እነዚህን ድሎች ለማንከባከብና ለመጠበቅ አስፈላጊ ለሆነው መስዋዕትነት ያለውን ዝግጁነት የተመለከቱ አድኃሪያን የትግላቸው ኃይል ያመዘነው እስከዚህም ፊት ለፊት በመጋፈጡ ላይ ሳይሆን አብዮታችንን በስተጀርባ ሆነው በመውጋቱ ላይ ነበር ።

አድኃሪያን አብዮታችንን ለመቀልበስ በስተጀርባ የመጡብን በመሠረቱ ተራማጆች ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች መስለው በሰፊው ሕዝብ ሰፈር ሰርገው በመግባት ነበር ። በዚህ በሰርጎ ገብነት ታክቲክ ተጠቅመው ትግሉን ጋብ አድርገው ፋታ ለማግኘትና እንዲያም ሲል ጨርሶ አብዮቱን ለመቀልበስ እንኳን በአብዮቱ ሠፈር ጥቂት የትግል ታሪክ ያላቸው የቀድሞ ተራማጅ ኃይሎች ይቅርና እነአስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ እንኳን በዚህ ዘዴ በሰፊው ለመጠቀም ሞክረዋል ። ነገር ግን እነዚህኞቹ የያዙትን ተራማጅ መሳይ መፈክር ይዘው ቢመጡ በተራማጆች ሠፈር ብዙም ዕድሜ እንደሌላቸው ያውቃሉ ። ስለሆነም ከተጠቀሙበት የቅልበሳ ታክቲኮች አንዱ በአብዮቱ ሠፈር አብዮታዊ መስሎ የሚያወናብድላቸውን ኃይል ጠቁመው እሱን ማገዝ ማጠናከርና በግንባር ቀደምነት ማሰለፍ ነበር ።

ከመጸነሱ ጀምሮ ለእንዲህ ዓይነቱ ሠርጎ ገብነት ራሱን አመቻችቶ የሰጠው የሠርጎ ገቦች አንጋፋ ቡድን የሆነው ኢሕአፓ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የአድኃሪያን ተራማጅ ኮከብ ሆኖ በሕዝቡ ሰፈር እንደቆየ እናውቃለን ። ነገር ግን ይህ ቡድን ፊታቸውን ገልጠው ፤ ዓላማቸውን አስታውቀው ከሕዝቡ ሰፈር ሊቆሙ ለማይችሉ አድኃሪ መፈክሮች የማርክሲዝም ሌኒንዝምን ካባ እያለበሰ በአብዮታችን ታሪክ አንድ የሠርጎ ገብነት ምዕራፍ ጻፈ እንጂ በአብዮታችን ሂደት አድኃሪዎች በዚህም በኩል ድል ከመመታት አላመለጡም ።

የየካቲትን አብዮታዊ ማዕበል አድኃሪያን ፊት ለፊት ሊቋቋሙት አልቻሉም ። የአብዮቱ ግስጋሴ ሰርጎ ገቦቻቸውን አጋልጦና ርቃን ሥጋቸውን አስቀርቶ ከሰፊው ሕዝብ ሠፈር አሽቀንጥሮ በመጣል መልሶ ወረወረላቸው ። አብዮታችንን በሶሻሊዝምና በአብዮት ስም ለመቀልበስ የተሞከረው ሴራ በተባበሩ ተራማጆች መራራ የርዕዮተ ዓለም ትግል ከሸፈ ። ሰርጎ ገቦችም በነሱና በተራማጅ ኃይሎች መሐከል ያለው ልዩነት በሰፊው ሕዝብ ወገኖች መሐከል ያለ ። በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ቀላል ልዩነት እንዳልሆነ ለማመን ተገደዱ ። ተወርውረው ከተጣሉበት ከአድኃሪው ሰፈራቸው ሆነው በአብዮታውያን ላይ አዲስ የፀረ አብዮት ትግል ምዕራፍ ከፈቱ ። ይኸውም የሽብር ፈጠራ ዘመቻ ነው ።

ይህ ከሁለት ወራት ወዲህ የተፋፋመው የሽብር ፈጠራ ዘመቻ አብዮታችን ግስጋሴ የፈጠረው ሁኔታ እንጂ ከሰማይ ዱብ ያለ መዓት አይደለም ። አድኃሪ ኃይሎች በሰፊው ሕዝብ መሃል እንደጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ዓይነቶቹን ቀልባሽ መፈክሮቻቸውን ይዘው ተመቻችተው እስከ ተቀመጡበትና በሕዝቡ ዘንድ ጥቂትም ብትሆን ተቀባይነት እስካገኙበት ወቅት ድረስ በሰርጎ ገብነት አብዮቱን የመቀልበስ ተስፋ ስለነበራቸው ሽብር ፈጠራን እንደትግል ዘዴ አይጠቀሙበትም ነበር ። አሁን ግን በስተጀርባ ሊያጠቁት ካልቻሉት አብዮቱ ጋር በርግጥም ተጻራሪ የሆነ ቅራኔ ውስጥ መግባታቸውን እንዲያምኑ ስለተገደዱ በግልጽ መሣሪያ ማንሳት የተገደዱበት ከፍተኛ የትግል ደረጃ ላይ ደርሰናል ።

በመሠረቱ ሽብር ፈጠራ የአብዮታውያን የትግል ዘዴ አይደለም ። በእንዲህ ዓይነቱ የተፋፋመ የትግልና የአብዮት ወቅት በዚህ ዘዴ ተሽቀዳድመው የሚሠማሩት አድኃሪ ኃይሎች ናቸው። በሩሲያ አብዮት ታሪክ ብንሄድ በግለሰቦች ግድያ አብዮትን ለመቀልበስ ሙከራ የጀመሩት ሶሻሊስት ሪቮሊሽነሪስ የተባሉ ንዑስ ከበርቴዎች ነበሩ። እነዚህ ንዑስ ከበርቴዎችና አናርኪስቶች በቦልሼቪኮች ላይ በግድያ ሙከራ፤ በማድረግ ፋብሪካዎችን በማቃጠል፤ ምርትን በማውደም፤ ድልድዮችን በመስበር ልዩ ልዩ አሻጥሮችን በመፈጸም አብዮቱ ገና ጨቅላ በነበረበት ወቅት ሊቀጩት ብዙ ሙከራዎች አድርገው ነበር ። በዚያንም ጊዜ አብዮታዊው የሩሲያ መንግሥት አድኃሪያን አንዲት የሽብር ድርጊት በሰነዘሩ ቁጥር ጠቅላላው የአድሃሪያን ሰፈር በሃላፊነት እንደሚጠየቅ አስታወቁ ። ለምሳሌ ሌኒንን ለመግደል ንዑስ ከበርቴዎች ሙከራ አድርገው ካቆሰሉት በኋላ የሶቪዬት መንግሥት ሽብርን ስለመቋቋም ጉዳይ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፎ ነበር ።

«በሶቪየት መንግሥት ሠራተኞችና ለሶሻሊስት አብዮት በሚታገሉ ሰዎች ላይ ለሚደረገው ማንኛውም የግድያ ሙከራ ጠቅላላውን አድኃሪዎችና እነሱንም የሚቀሰቅሱት ሁሉ በኃላፊነት ይጠየቃሉ።

የወዝአደሩና የአርሶ አደሩ መንግሥት ጠላቶቹ ለሚሠነዝሩበት አድኃሪ ሽብር አጸፋውን በመመለስ በከበርቴውና በወኪሎቹ ላይ አጠቃላይ የሆነ አብዮታዊ ሽብር ይለቅባቸዋል » ይላል ።

እነሌኒን የአድኃሪዎችን ሽብር ፈጠራ ለመቋቋም በተከላካይነት ደረጃ የመቀመጥን አደገኛነት የተገነዘቡ አብዮታውያን ነበሩ ። በተከላካይነት ደረጃ ተወስኖ ወደፊት የተራመደ አብዮት የለም ።

ስለሆነም ሽብርን ለመቋቋም አብዮታችን ወደአጥቂነት ደረጃ መሸጋገር አለበት ። ይህንን ማድረግ የተሳነው ፤ « ዛሬ ደግሞ አድኃሪዎች የት ይመቱ ይሆን? » እያለ የነሱን ጥቃት ለመ ከላከል የሚያደባ አብዮት ወደፊት መራመድ አይቻልም ።

በዚህ መስክ አብዮቱ ወደአጥቂነት ደረጃ ሊሸጋገር የሚቻለው የሰፊው ሕዝብና የአብዮታውያን የተቀነባበረ ተሳትፎ ሲኖር ብቻ ነው ። ሰሞኑን እየተደጋገሙ የሚነሱት የየመን ሕዝባዊ ዲሞክራሲ ያዊ ሪፐብሊክና የኩባ ሶሻሊስት መንግሥት «የአብዮት ተከላካይ ኮሚቴዎች» ለኢትዮጵያ አብዮት ትልቅ ትምህርት የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ በሁለቱ አገሮች የቀልባሾችን አሻጥር፤ የአድኃሪያንን ሽብ ርና በትጥቅ የተደገፈ የቅልበሳ ሙከራ ለማክሸፍ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ «የአብዮት ተከላካይ ኮሚ ቴዎች» በየፋብሪካው፤ በየእርሻ መስኩ፤ በየቀበሌው...ተቋቁመው በተቀነባበረ ዘዴ አድኃሪ ኃይሎችን በያሉበት ከቁጥጥራቸው ሥር አውለው ደምስሰዋቸዋል።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ አድኃሪዎች በተሰገሰጉባቸውና የሽብር ፈጠራ ትግላቸውን ባፋፋሙባቸው ከተማዎች የከተማ ኗሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት የቀበሌውን ሕዝብ ኑሮ ከማሟላትና ከማስተዳ ደር ሚና አልፈው አብዮቱን ከቀልባሾችና ከአሸባሪዎች ለመከላከል የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ያስፈልጋል ። በየሠፈሩ ያሉትን አድኃሪዎች ከሠፈርተኛው ይበልጥ፤ በየፋብሪካው ያሉትን አድኃሪዎች ከወዝአደሩ ይበልጥ ለይቶ የሚያውቃቸው ኃይል የለም ። ስለሆነም በአድኃሪ ኃይሎች ላይ በየጊዜው ተገቢውን ርምጃ ለመውሰድ እንዲችሉ በአብዮት ተከላካይ ኮሚቴዎች አማካይነት የተደራጁ የቀበሌ ኗሪዎችና የፋብሪካ ወዝአደሮች በትጥቅ ብቁ ሆነው ግዴታቸውን ቢፈጽሙ አብዮታችንን ከቀል ባሾችና ከሽብር ፈጣሪዎች ለመከላከል ይቻላል ። ይህ እስካልሆነ ድረስ ግን፤ ሰፊው ሕዝብ ተደራጅ ቶና ታጥቆ ካልተሳተፈበት አብዮቱ በሽብር ፈጣሪዎች ላይ በአጥቂነት ደረጃ ሊሰለፍ አይችልም ። በአጥቂነት ደረጃ ሳይሰለፍ ሽብርን ለመመከት ብቻ እስከተወሰነ ድረስ አንድ አብዮት የመዝረክረ ክና የመቀልበስ ዕድል ሊያጋጥመው ይቻላል።

ሰፊው ሕዝብ ይታጠቅ

አብዮታዊት ኢትዮጵያ